# በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ማንዋል የአጋር አካላት ተሳትፎ

የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን

ጥር 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE

## በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የአጋር አካላት ተሳትፎ የፍትህ ሚኒስቴር ማንዋል

ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የሽግግር ሂደቶች ውስጥ ያለፈች ቢሆንም በፖሊሲ የተመራ የሽግግር ፍትህ ሂደት ተግባራዊ ያልተደረገ በመሆኑ ውጤታማ የሆነ የሽግግር ሂደት ሳይደረግየቀየ መሆኑን ከግምት በማስገባት የሽግግር ፍትህ ሂደት በሀገርአቀፍ ደረጃ በምን አግባብ መመራት አለበት የሚለውን እና መሰል ጥያቄዎችን የሚመልስ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ለማዘጋጀት በፍትህ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የባለሙያዎች ቡድን ተደራጅቶ እንቅስቃሴ የጀመረ በመሆኑ፣

በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ የአጋር አካላት ተሳትፎ ሲሆን በአሁኑ ሰአትም ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ የድጋፍ ጥያቄዎች ከተለያዩ አጋር አካላት እየመጡ በመሆኑ እና የአጋር አካላት የድጋፍ ተሳትፎ የሚመራበትን ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን በተለያየ መንገድ የሚደግፉ አካላት፣ በዝግጅት ሂደቱ የሚኖራቸው የተሳትፎ ደረጃ እና ሁኔታን በግልፅ ሥርዓት ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ፍትህ ሚኒስቴር በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀፅ 21(2) መሰረት ይህንን ማንዋል አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ማንዋል "የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የአጋር አካላት የድጋፍ ተሳትፎ ማንዋል ቁጥር-----/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ማንዋል ውስጥ፡-

1) “ፖሊሲ” ማለት በፍትህ ሚኒስቴር የተደራጀው የባለሙያዎች ቡድን የሚያዘጋጀው ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ነው፤

2) “የባለሙያዎች ቡድን” ማለት የሽግግር ፍትህ ረቂቅ ፖሊሲ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ከተለያዩ አካላት የተውጣጡ አባላትን እንዲይዝ ተደርጎ በፍትህ ሚኒስቴር የተደራጀው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ አዘጋጅ የባለሙያዎች ቡድን ነው፤

3) “ሚኒስቴር” ማለት የፍትህ ሚኒስቴር ነው፤

4) “አጋር” ማለት ለሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ስራ ድጋፍ ማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ነው።

5) “ድጋፍ ማድረግ ” ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ወጪን ለመሸፈን የሚውል ድጋፍ ለሚኒስቴሩ መስጠት፣ ከዝግጅቱ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ወጪዎችን ክፍያ በቀጥታ አገልግሎቱን ለሰጡ አካላት መፈጸም፣ ሙያዊ እገዛ ማድረግ፣ ስራውን የሚያግዙ ባለሙያዎችን ማፈላለግና መመደብ፣ ለባለሙያዎች ቡድን ክፍያ መክፈል፣ ከስራው ጋር በተያያዘ በባለሙያዎች ቡድን የተዘጋጁ ሰነዶች ላይ በፅሁፍ አስተያየት መስጠት፣ ለዝግጅቱ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ለባለሙያዎች ማቅረብ እና የመሳሰሉት ተግባራትን ማከናወን ነው፤

6) “የበላይ አመራር” ማለት የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይም የመንግስት ሕግና ፍትህ አገልግሎት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ነው፤

7) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም አካል ነው፤

8) በወንድ ፆታ የተመለከተው አገላለፅ የሴትንም ፆታ ያካትታል።

3. **የማንዋሉ ዓላማ**

ማንዋሉ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

1) በሽግግር ፍትህ ሂደት ድጋፍ ለማድረግ የሚፈልጉ ወይም ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ባለ ድርሻ አካላትን አካላት በሚኒስቴሩ እና በመንግስት ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት ላይ ጣልቃ መግባትን በማያስከትል ሁኔታ ግልጽና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚለዩበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

2) የእያንዳንዱ ባለ ድርሻ አካል ድጋፍ በምን አግባብ መሆን እንዳለበት መለየት እና ስርዓት ማስያዝ፤ የድጋፍ ሰጭ አካላትን የድጋፍ ጥያቄ አቀራረብ፣ የድጋፍ አሰጣጥ እና ድጋፍ ሰጭ አካላት ከሚኒስቴሩና ከባለሞያዎች ቡድን ጋር ሊኖራቸው የሚገባ የግንኙነት ሥርዓት መዘርጋት፣ እንዲሁም አጋር አካላት በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የሚኖራቸውን የተሳትፎ ሁኔታ እና ደረጃ ማመልከት።

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ማንዋል በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ድጋፍ በሚያደርግ ተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የድጋፍ ሰጭ አካላት የድጋፍ ተሳትፎ እና የግንኙነት አግባብ

5. **ድጋፍ ስለማድረግ**

1) የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደትን ለመደገፍ ፍላጎት ያለው ማንኛውም በሚኒስቴሩ ድጋፍ እንዲያደርግ የተጠየቀ ወይም ድጋፍ ለማድረግ ጠይቆ የተፈቀደለት ሰው ድጋፍ ማድረግ ይችላል።

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተደነገገው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የድጋፍ ስርዓቱ በሚከተለው አግባብ የሚተገበር ይሆናል፡-

ሀ/ ፖሊሲው እና ፖሊሲውን ተከትሎ የሚዘጋጁ ማናቸውም የሕግ ሰነዶች የሚዘጋጁት ሚኒስቴሩ በሚመድባቸው ባለሙያዎች ብቻ ይሆናል፣

ለ/ ሚኒስቴሩ ድጋፍ እንዲያደርግ የጠየቀው ማንኛውም አካል፣ ከዚህ በፊት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር የድጋፍ ትብብር ግንኙነት የነበራቸው የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገርድጋፍ ሰጭ አካላት እና ሌሎች ሚኒስቴሩ ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚፈቅድላቸው አካላት የዝግጅት ሂደቱን በቀጥታ ለሚኒስቴሩ ድጋፍ በመስጠት፣ የተለያዩ የባለሙያዎችን እና ሌሎች በሂደቱ የሚሳተፉ አካላትን ወጪዎች እና ሌሎች ሚኒስቴሩ እንዲከፈሉ የሚጠይቃቸውን ከሂደቱ ጋር የተያያዙ ወጪዎች በቀጥታ በመሸፈን ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ፣

ሐ/ ማንኛውም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ ድጋፍ ሰጭ አካል በባለሙያዎች ቡድን የተዘጋጁ ሰነዶችን በመውሰድ በሰነዶቹ ላይ ያለውን አስተያየት በፅሁፍ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፣

መ/ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ ድጋፍ ሰጭ አካል በቡድኑ በተዘጋጁ ሰነዶች ላይ አስተያየት የሚሰጡ ወይም ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጃቸው የውይይት መድረኮች ላይ በመገኘት ግብአት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ወጪዎቻቸውን በመሸፈን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲመጡ ወይም ባሉበት ሆነው ሙዊ ድጋፍ በማድረግ እንዲሳተፉ ማድረግ ይችላል፣

## 6. የድጋፍ ሥርዓት እና የአጋር አካላት ሚና

1) ማንኛውም በዚህ ማንዋል አንቀፅ 5 መሰረት ድጋፍ የሚያደርግ አጋር አካል ድጋፉን በቀጥታ ለሚኒስቴሩ በመስጠት ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ሊያስፈፅም ይችላል፣

2) ማንኛውም አጋር አካል፣ በዚህ መመሪያ መሰረት ድጋፍ ለሂደቱ ድጋፍ ማድረጉ፣ በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱ ላይ በተለየ መልኩ የመሳተፍ መብት አያስገኝለትም፣

3) በዚህ ማንዋል አንቀፅ 5 መሰረት ድጋፍ እንዲያደርግ በሚኒስቴሩ የተጠየቀ ወይም ድጋፍ ለማድረግ ጠይቆ የተፈቀደለት አጋር አካል ድጋፍ ስለሚያደርግበት ዝርዝር ሂደት እና ሥርዓት ከስራ ቡድኑ ሰብሳቢ ጋር በመነጋገር ይፈፅማል፣

## 7. ድጋፍ ማድረግ ስለሚችሉ አካላት

1) በዚህ ማንዋል አንቀፅ 5 መሰረት ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ከዚህ በፊት በተለያየ መንገድ በሽግግር ፍትህ፣ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር፣ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እና መሰል ትግባራት ላይ ሲሰሩ የነበሩ ዓለማቀፍ እና ሀገር አቀፍ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የተለያዩ ሀገራት ኢምባሲዎች፣ የተባበሩት መንግስታት እና የአፍሪካ ህብረት የስራ ክፍሎች ወይም ቅርንጫፎች እና የመሳሰሉት ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ፣

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኑ ድጋፍ ማድረግ የሚችሉ አካላትን የመለየት እና የመወሰን ኃላፊነት የከፍተኛ አመራሩ ይሆናል፣

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የስራ ቡድን አባላት ድጋፍ ሊያደርጉ ስለሚችሉ አጋር አካላት ምክረ ሀሳብ ለከፍተኛ አመራሩ ማቅረብ ይችላሉ።

## 8. የግንኙነት አግባብ

1) ማንኛውም በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱ ላይ ለመሳተፍ ወይም ድጋፍ ለማድረግ የሚፈልግ አካል ድጋፍ ስለሚያደርግበት አግባብ መደበኛ ንግግር ወይም ውይይት ማድረግ የሚችለው ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበላይ አመራሮች ጋር ይሆናል፣

2) ድጋፍ ለማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም አካል የድጋፍ ጥያቄውን አመቺ በመሰለው መንገድ ማቅረብ ይችላል፣ ሆኖም ጥያቄውን በኢሜል ማቅረብ ከፈለገ ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው የኢሜል አድራሻ በኩል ስለማንነቱ፣ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችለው መነሻ ምክንያት እና ድጋፍ ስለሚያደርግበት አግባብ በመግለፅ ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል፣

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ጥያቄውን በኢሜል የተቀበለ የባለሙያዎች ቡድን አባል ለጥያቄው ምላሽ ከመስጠቱ በፊት ጥያቄው የቀረበ ስለመሆኑ ለከፍተኛ አመራሩ የማሳወቅ እና ከፍተኛ አመራሩ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፣

4) በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ (1-3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚኒስቴሩ የበላይ አመራር የባለሙያዎች ቡድን ከድጋፍ ሰጭ አካል ጋር ስለድጋፍ ሥርዓት እንዲነጋገሩ ትዕዛዝ በሰጠ ጊዜ የባለሙያዎች ቡድን ከድጋፍ ሰጭ አካል ጋር ስለድጋፍ ሥርዓቱ ይነጋገራል፣ ስለሁኔታው ለበላይ አመራሩ መረጃውን ይሰጣል፣

5) የበላይ አመራሩ እና ድጋፍ ሰጭ አካል ስለድጋፍ ሥርዓቱ ከተወያዩ በኋላ በሂደቱ ድጋፍ እንዲያደርግ የተፈቀደለት ድጋፍ ሰጭ አካል በየጊዜው ከባለሙያዎች ቡድን ጋር በመገናኘት በተፈቀደለት አግባብ ዝርዝር ተግባራትን ማከናወን ይችላል፣

6) በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ (1-5) የተደነገጉት ቢኖሩም የባለሙያዎች ቡድን የበላይ አመራሩ ፍቃድ ሳያስፈልገው የተዘጋጁ እና ለህዝብ ውይይት የቀረቡ ሰነዶችን አግባብ ናቸው ብሎ ላመነባቸው የሀገር ውስጥ እና የውጪ ሀገር ባለሙያዎች በመላክ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ማድረግ ይችላል።

**ክፍል ሶስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

9. **የማንዋሉ የአፈፃፀም ሁኔታ**

ይህ ማንዋል ከሚኒስቴሩ ሌሎች ማንዋልዎች እና የአሰራር ሥርዓቶች ጋር በተናበበ እና በተስማማ መልኩ ተፈፃሚ ይደረጋል።

10. **ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ልማዳዊ አሰራሮች**

ከዚህ ማንዋል ጋር የሚቃረን ማንኛዉም የአሰራር ልምድ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና ፖሊሲውን ተከትለው የሚዘጋጁ የህግ ሰነዶችን በተመለከተ በዚህ ማንዋል በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም።

11. **ማንዋሉ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ማንዋል በፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ፣ የካቲት …… ቀን 2015 ዓ/ም**

**ጌዲዮን ጢሞቲዮስ(ዶ/ር)**

**ሚኒስትር**